# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 220 ሐምሌ 26 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የማጭበርበርን ባህል ከመለስ ዜናዊ ሥርዓት ጋር ካልቀበርነው በስተቀር ለትውልድና ለሃገር እድገት እጅግ ከፍተኛ እንቅፋት መሆኑ የማይቀር ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በማጭበርበር ባህል ላይ የተገነባው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በአጭር ጊዜ ለማስወገድ ተግቶ ይሠራል።

መለስ ዜናዊ እያጭበረበረ ኖራል፤ ሞቶም እንዲያጭበረብር ግን ፈጽሞ አንፈቅድለትም። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት ኢሳት ከዘገበ ቦኋላ በረከት ስምኦን ዜናውን አሉባልታ ነው ሲል ለማጣጣል እንደሞከረ ታወቀ። ኢሳት ግን አሉባልታ ነው ከምትሉን ሚቹን አሳዩንና ሞግቱን ሲል አሳሰበ

የዘረኛው መለስ ዜናዊን በጸና መታመም ዜና እርስ በርሱ በሚጋጭ መግለጫ ውሸት ነው በማለት ሲያስተባብል የቆየው የወያኔ አገዛዝ በኮሚኒኬሽን ሚንስተሩ ስምዖን በረከት አማካኝነት ስለ መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት መለየት የተዘገበው ዘገባ በመተግበር ላይ ያለውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማደናቀፍ አፍራሽ ሃይሎች የሚነዙት አሉባልታ ነው የሚል መግለጫ መስጠቱ ተዘገበ።

በረከት ስሞን በትናንትናው ዕለት በወያኔ ቁጥጥር ሥር በሚተዳደረው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴለቪዥ በሰጠው መግለጫ እንደተናገረው የአምስት አመቱን የልማትና ዕድገት ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መተግበር ከተጀመረ ሁለት አመት እንደሆነውና የህብረተሰቡ ተሳትፎም ከፍተኛ መሆኑን የሚያመለክተው ለሂዳሰ ግንባታ ለተባለው የአባይ ግድብ ህዝቡ እያሳየ ያለው መረባረብ ነው።

መንግሥትና ህዝብ በልማት ዕቅዱ ላይ መረባረባቸውን ለማሰናከል የሚንቀሳቀሱ አፍራሽ ሃይሎች መንግሥት የህዝቡን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ነው የሂዳሰውን ግድብ የተያያዘው የሚል አሉባልታ ሲያናፍሱ እንደቆዩት ሁሉ ከሰሞኑ ደግሞ የጠቅላይ ሚንስትሩን ጤንነት አስመልክቶ ሌላ አሉባልታ እያናፈሱ ነው በማለት ጠቅላይ ሚንስትሩ ሞቶአል ተብሎ በመላው አገሪቱ ውስጥ የሚወራውን ወሬ በትክክል ሳይገልጽ በድፍኑ አድበስብሶ ለማለፍ የሞከረው በረከት ስለ አለቃው ጤንነት ከራሱ ጋዜጠኞች ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው ምላሽ ማንንም ለማሳመን እንዳልቻለ ይነገራል።

በረከት ስሞን ባለፈው ሁለት ሳምንት በሰጠው አፊሰላዊ መግለጫ ለምን ስለ መለስ ዜናዊ ህመም ለህዝብ እንዳልተገለጸ ተጠይቆ የሰጠው ምላሽ በቆየው የኢሃአደግ አሰራር እንዲህ አይነት ዜናዎችን ይፋ ማድረግ እንዳልተለመደና ህዝብም መጠበቅ የሌለበት መሆኑን ነበር። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአዲስ አበባ እንደ ወረርሽኝ በመጡት የእርቃን ዳንስ ቤቶች የመንግስት ባለስልጣናት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስራ ሀላፊዎች፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላትና ነጋዴዎች ዋነኛ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን አንድ ጥናት ይፋ አደረገ

በአዲስ አበባ መስተዳድር የተቋቋመ አንድ የጥናት ቡድን ሪፖርት እንደገለጸው የእነዚህ እርቃን ዳንስ ቤቶች ዳንሰኞች አብዛኞቹ የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንዲሁም ከሞዴሊንግ ማሰልጠኛ ተቋማት የተመረቁ ወጣቶች ናቸው።

በጥናቱ በዚህ ስብእናንና ክብርን በሚነካ ድርጊት በተለያዩ እርከኖች ከሚገኙ ሀላፊዎች ሌላ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው ግለሰቦች፣ ባለሀብቶችና ባለሙያዎች ተሳታፊ መሆናቸው ተገላጿል።

ለችግሮቹ መከሰት ስራ ማጣት፣ የወጣቶች አለመማር፣ የቤተሰብ መፍረስ፣ የትምህርት ቤቶችና የወላጆች ቁጥጥር መላላት ዋነኛ ማህበራዊ ምክንያቶች መሆናቸውን የጠቀሰው ጥናቱ ተስፋ ማጣትን፣ ያለስራ መቀመጥን፣ ዘመናዊ መስሎ ለመታየት መሞከርን፣ የራስ ባህልን መናቅና ጠንቅቆ አለማወቅን በስነ ልቡና፤ ራስን ለመደገፍ የኢኮኖሚ አቅም ማጣትን፣ የኤኮኖሚ ጥገኝነትን፣ የሀብት መብዛትና ማነስን በኢኮኖሚ ምክንያትነት በማንሳት አብራርቷል።

ጥናቱ በተጨማሪም በየህንጻዎቹ ስር፣ በየመንገዶቹ ዳርና በየመኪና ማቆሚያ ቦታዎች የሚፈጸሙት በመኪና ውስጥ ጫት መቃምና የወሲብ ድርጊቶችን መፈጸም አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ጠቁሞ ድርጊቱን የሚፈጽሙት በአብዛኛው ህጻናትና ወጣቶች ቢሆኑም፣ በእድሜ የበሰሉ ሰዎችም እንደሚገኙበት አስረድቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በወቅቱ የአገራችን ጉዳይ ላይ ቅድሚያ በመስጠት የተነጋገረው የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አመታዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱ ተገለጸ

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ካለፈው አርብ ሃምሌ 22 እስከ ሃምሌ 24 ቀን 2004 ድርስ ባካሄደው የንቅናቄው አመታዊ ስብሰባ በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ በስፋት በመነጋገር በአስቸኳይ ሊተገበሩ ይገባቸዋል ባላቸው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማስተላለፉን የንቅናቄው የህዝብ ግንኙነት ለዝግጅት ክፍላችን በላከው ማስታወሻ ገለጸ።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላለፉት 21 አመታት የተገበራቸው የዘረኝነት ፖሊሲዎች በህዝባችን መሃል የፈጠራቸው ብሶትና ምሬቶች ፈንድተው የአገዛዙን ዕድሜ ለማሳጠር ለሚደረገው የነጻነት ትግል ምቹ ሁኔታዎች በፈጠሩበት በአሁኑ ሰዓት የተካሄደው ይህ የግንቦት 7 አመታዊ ስብሰባ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከተነጋገረባቸውና ውሳኔ ካሳለፈባቸው ጉዳዮች አንዱ ከወያኔ ሥርዓት መደምሰስ በኋላ ሊፈጠር ስለሚገባው የሽግግር ወቅትና በአገራችን ሊመሰረት ስለሚገባው የዲሞክራሲ ሥርዓት መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

ንቅናቄው በዚህ አመታዊ ስብሰባው የወቅቱ የአገራችን ሁኔታ የፈጠረውን ስጋት ለማስወገድ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት ሁሉ በቁርጠኝነት ለመወጣት ዝግጁ እንደሆነና በምድር ላይ የሚያካህደውን ትግል ከሌሎች ተመሳሳይ የትግል ስልት ከሚከተሉ ድርጅቶች ጋር በመሆን ለማፋጠን እንደወሰነ አሳውቆአል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በፈጠረው ጸረ ኢትዮጵያዊ ጥቃት ከአገራቸው ይልቅ ለባ ዕድ አገር መሰለፍን የመረጡ አትሌቶች ቁጥር አስደጋጭ መሆኑን የዘንድሮው የሎንዶን አሎሚፒክ አጋለጠ

ባለፈው አርብ ሃምሌ 22 ቀን ሎንዶን ላይ በተከፈተው የዘንድሮው የኦሎምፒክ ውድድር ላይ አገራቸውን ትተው ለሌላ አገር የተሰለፉ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ቁጥር እጅግ አስደንጋጭ መሆኑን በአመሪካን አገር በሚኒሶታ የሚታተም ዘ-ሐባሻ የተባለ ጋዜጣ ይፋ ካደረገው ሥም ዝርዝር ለማወቅ ተችሎአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወደስልጣን ከመጣበት 1983 ወዲህ አገራቸውን ትተው የሚሰደዱ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ከመንግሥት አልባዋ ሱማሌና በጦርነት ከምትታመሰው አፍጋንስታን የሚወዳደር ሲሆን አለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተሚጋች ድርጅት ሲፒጄ ከአገራችን የሚሰደዱ ጋዜጠኞችን ቁጥር በአለም አቀፍ ደረጃ አንደኛ እንደሆነ ሲዘግብ መቆየቱ ይታወቃል።

በዘንድሮው የሎንዶን ኦሎምፒክ ኢትዮጵያ ካሰለፈቻቸው አትሌቶች ቁጥር በእጥፍ የሚበልጡቱ አገራቸውን ትተው ለባዕዳን አገር እንደሚወዳደሩ መታወቁ በሁሉም ዘርፍ አገራቸውን ትተው የሚሰደዱ ዜጎች ቁጥር ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነና ይህም ወያኔ አገራችንን ለማጥፋት ላለፉት 21 አመታት ያካሄዳቸው ተግባራት ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ አመላካች ሆኖአል።

የባዕዳን አገሮችን ወክለው በሎንዶኑ ለመወዳደር ዘንድሮ የተሰለፉ አትሌቶቻችን ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ የተነሳ ኢትዮጵያን ወክለው ለመወዳደር የተላኩ አትሌቶቻችን የሚፎካከሩት ከሌሎች አገራት አትሌቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ዜግነታቸውን ከቀየሩ የአገራቸው ልጆች ጋር መሆኑ የዘ-ሐባሻ ጋዜጣ አዘጋጅ ሔኖክ ዓለማየሁ በጋዜጣው አስፍሮአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተቀሰቀሰዉ የጎሳ ግጭት አሁንም እልባት አላገኘም - በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች አካባቢዉን እየጣሉ ወደ ጎረቤት አገሮች እየተሰደዱ ነዉ

ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በሚኖሩት በኦሮሞ ብሔረሰብና ጋሪ በሚል መጠሪያ በሚታወቁት ኢትዮጵያዉያን የሶማሊያ ተወላጆች መካከል የተቀሰቀሰዉ የጎሳ ግጭት ከሰላሳ በላይ ሰዎችን መግደሉንና ከሃያ ሺ በላይ የአካባቢዉን ነዋሪዎች ለስደት መዳረጉን አለም አቀፉ የቀይ መስቀል ድርጅትና ቢቢሲ የተሰኘዉ የእንግሊዝ ሬዲዮ አስታወቁ። በዚህ መሳሪያ በታጠቁ በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል በተቀሰቀሰዉ ግጭት የሞቱት ሰዎች ብዛት ሰላሳ የደረሰ ሲሆን የቆሰሉና ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ እንደሆነ ቢነገርም ቁጥራቸዉ ቁጥራቸዉን በዉል ለይቶ ማወቅ አልተቻልም፤ ሆኖም በግጭቱ አንድ የፌዴራል ፖሊስ መገደሉንና ሰባት የክልሉ ፖሊሶች መቁሰላቸዉን ግጭቱን ለመከታተል ወደ ስፍራዉ የተጓዘዉ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ የላከልን ዜና ያስረዳል፡፡

የጋሪ ሶሞሌና የቦረና ኦሮሞ ብሔረሰቦች የሚኖሩበት አካባቢ ለኢትዮጵያ፤ ለኬንያና ለሶማሊያ የድንበር አካባቢዎች የቀረበ ነዉ። በእነዚህ የድንበር አካባቢዎች የሚኖረዉ ህዝብ በተለይ በክብት ርቢ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ማጭበርበር - የመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ብሄል መሠረት

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በማጭበርበር ተወልዶ፤ በማጭበርበር አድጎ፤ እያጭበረበረ ወደ መቃብር በመንጎድ ላይ ይገኛል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ እና ማጭበርበር በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው። መለስ ዜናዊ በእርዳታ ስም አጭበርብሯል፤ በእድገት ስም አጭበርብሯል፤ በፍትህ ስም አጭበርብሯል፤ በዲሞክራሲ ስም አጭበርብሯል። ሌላው ቀርቶ በበሽታና በሞትም እያጭበረበረ ነው።

### ማጭበርበር በበረሃ

ትግራይን ነፃ የማውጣት ዓላማ አንግቦ የተነሳው እና በመለስ ዜናዊ ሲመራ የነበረው ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ሕወሃት) በበረሃ በነበረት ወቅት ከፍተኛ ማጭበርበሮችን ፈጽሟል። ሕወሃት በረሃ እያለ ጀምሮ አሸዋ የሞሉ ከረጢቶችን እህል ነው እያለ ለእርዳታ ድርጅቶች በመሸጥ የማጭበርበር ልምድ ያካበተ ድርጅት ነው። በድርቅ ለተጎዳ ሕዝብ የመጣውን እርዳታ በአግባቡ አከፋፍላለሁ እያለ ለእርዳታ ሰጪዎች እየተናገር በተግባር ግን 55 በመቶው ለማሌሊት ማጠናከሪያ፤ 40 በመቶው ለቀይ ሠራዊት፤ እና 5 በመቶው ደግሞ ለተረጂዎቹ ማከፋፈሉ የቀድሞ አባላቱ፤ የብርታኒያ የዜና ወኪል (ቢቢሲ) እና በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ በርካታ ተቋማት ያረጋገጡት ሃቅ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሕወሃት በረሃ ውስጥ እያለ በርካታ የፓለቲካ ማጭበርበሮችን ሲፈጽም የኖረ ድርጅት ነው።

### ማጭበርበር በአራት ኪሎ

ወያኔ ምኒሊክ ቤተመንግሥት በጉልበት ከገባም ወዲህ ሥልጣኑን የዘረጋው በማጭበርበር ነው። ስለእኩልነት እየተናገረ ዘረኛ የሆነ ሥርዓት ገንብቷል። “የመሬት ጉዳይ በመቃብሬ ላይ” እያለ በሄክታር ከአስር ዶላር ባነሰ የሊዝ ዋጋ ለራሱ ወገኖች፣ ለቱጃር አረቦችና ህንዶች ለም መሬት ሲቸበችብ ኖሯል። ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ግድብ፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ኮንዶሚኒየም፣ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክ ወይም ሌሎች ግንባታዎች ሁሉ ሕዝብንና እርዳታ ሰጪዎችን የማጭበርበሪያ መሣሪያዎች ናቸው።

### ማጭበርበር በፓርላማ

ወያኔ በምርጫ ማጭበርበር “ጥበብ” ከፍተኛ “የብቃት” ደረጃ ላይ የደረሰ ድርጅት ነው። ይህንን የላቀ የሌብነት ችሎታውን በምርጫ 97 ማግሥት በተግባር ላይ አውሎታል። ሕዝብ “ወያኔ ድምፅ ዘረፈን” በማለት አቤቱታ ሲያቀርብ፤ ወያኔ ደግሞ “ተቃሚዎች ድምፅ ዘረፉኝ” በማለት የሚያማርር ዓይን ዓውጣ አጭበርባሪ ድርጅት ነው። ነፃ፣ ግልጽና ፍትሃዊ ምርጫ አካሂጃለሁ እያለ በማጭበርበር 99.6 በመቶ የፓርላማ ወንበሮችን ይዞ ስለዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ይደሰኩራል። የአዋጅ ረቂቆችን በማንበብም “በውይይት ዳበሩ” እያሉ ያጭበረብራል።

### ማጭበርበር በሆስፒታል አልጋ

መለስ ዜናዊ የአልጋ ቁራኛ በሆነባቸው ጥቂት ወራት ውስጥም የቆየው በማጭበርበር ነው። ታሞ አልታመመም፤ አልታመመም ተብሎ ታመመ ይባላል። መለስ ዜናዊ ሰውነቱ ቢዝልና አንደበቱ ቢታሰር እንኳን መዋሸት አይቸግረውም። መለስ ዜናዊ ያቆመው ሥርዓት እራሱ መለስ ዜናዊ ሞቶም ቢሆን ማጭበርበሩን የሚተው አይደለም።

የማጭበርበርን ባህል ከመለስ ዜናዊ ሥርዓት ጋር ካልቀበርነው በስተቀር ለትውልድና ለሃገር እድገት እጅግ ከፍተኛ እንቅፋት መሆኑ የማይቀር ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በማጭበርበር ባህል ላይ የተገነባው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በአጭር ጊዜ ለማስወገድ ተግቶ ይሠራል።

መለስ ዜናዊ እያጭበረበረ ኖራል፤ ሞቶም እንዲያጭበረብር ግን ፈጽሞ አንፈቅድለትም።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.................................................................................................................................................................................................

## የመለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት ኢሳት ከዘገበ ቦኋላ በረከት ስምኦን ዜናውን አሉባልታ ነው ሲል

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊ ጤንነት በከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኑንና በህይወት ለመቆየት ከ3ወር ጊዜ የበለጠ ተስፋ እንደሌለው መረጃው በህብረተሰቡ ውስጥ በሰፊው ተሰራጭቶ እያለ ሰውዬም እረፍት ላይ ነው የሚል የሃሰት መግለጫ ሲያዝጎደጉድ የሰነበተው ፖሮፖጋንዲስቱ በረከት ስምን የመለስን መታመም የሚያስወሩት የመረጋጋት አደጋ እንዲፈጠር የሚፈልጉ ሃይሎች ናቸው ሲል ሃይማኖትንም እንደ ስልት ይጠቀማሉ ሲል ተሰምቶአል።

ይህ በዚህ እንዳለ የ መለስ ዜናዊን ከዚህ አለም በሞት መለየት ዜና የዘገበው ኢሳት በትናንትናው ዕለት ለበረከት ስሞን መግለጫ በሰጠው ምላሽ በህይወት አለ የምትሉ ከሆነ የድምጽ ወይም የቪዲዮ ምስሉን አቅርቡና አሳዩን ሲል ጥያቄ ማቅረቡን ለማወቅ ተችሎአል።

በረከት ስሞን ሪፖርተርና ሰንደቅ ለተባሉት ጋዜጦች እንዲሁም ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የኢሳትን ዜና በማስተባበል መግለጫ በሰጠው መግለጫ " እነዚህ ሀይሎች የሀሰት ወሬ በሀገራችን ላይ ሲያሰራጩ ዛሬ የመጀመሪያቸው አይደለም። በተለይም በሰሜን አፍሪካ ውስጥ የተፈጠረውን የፖለቲካ ትርምስ ተከትሎ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው እውነታ ውጪ፣ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መንዛት ስራቸው አድርገውት ከርመዋል። የእነዚህ ሀይሎች አላማ አንድ እና አንድ ብቻ ሲሆን፣ ይህውም ያልተጫበጠ መረጃ በማሰራጨት ህብረተሰቡን ወደ ትርምስ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ነው። ይህ ከሰሜን አፍሪካ የፖለቲካ ቅጥያ የትርምስ ስትራቴጂያቸው አልሰራ ስላላቸው በአዲስ መልክና ስልት አሁን መምጣታቸው ይሆናል።" ማለቱን ጠቅሶአል።

በረከት በሪፓርት ጋዜጣ ላይ ለማንኛውም አሉባልታ መግለጫ አንሰጥም በማለት ከተናገረ በሁዋላ ውሎ ሳያድር ለኢትዮጵያ ቴሌቪዢን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት መገደዱ ኢሳት የፈጠረበት ጫና ነው ያለው የኢሳት ኢዲቶሪያል ቦርድ “የኢትዮጵያ መንግስት ላለፉት ሁለት አመታት ለኢሳት እውቅና ላለመስጠት ሲል እናቀርብ ለነበረው ዘገባዎች መልስ ሰጥቶ አያውቅም ብሎአል። ቦርዱ አክሎም፣ ከዚህ ቀደም የኤርትራው ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ እና የዝምባብዌ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሮበርት ሙጋቤ ሞተዋል የሚል ዜና በአለማቀፍ መገናኛ ብዙሀን ሳይቀር ሲተላለፍ፣ ሁለቱም መሪዎች ወደ አደባባይ በመውጣት በሙሉ ጤንነት ላይ መሆናቸውን ማሳየታቸውን አስታውሷል። ኮሚኒስት አገር በምትባለዋ ኩባ እንኳን የጓድ ፊደል ካስትሮ የጤና ሁኔታ ለህዝቡ በየጊዜው ይፋ ይደረግ ነበር ያለው ቦርዱ፣ የኢትዮጵያ መንግስት ገዢው መታመማቸውን እንኳ አምኖ የተቀበለው ዜናው በኢሳት እና በሌሎች አለማቀፍ መገናኛ ብዘሀን ከወጣ በሁዋላ ነው ብሎአል። ይህም መንግስት የሚመራውን ህዝብ ምን ያክል እንደሚንቀውና ምን ያክል በጨለማ ውስጥ አኑሮ ሊገዛው እንደሚፈልግ ያሳያል ብሎአል።

የኢሳት ኢዲቶሪያል ቦርድ የኢትዮጵያ መንግስት አንድ ጊዜ በቃል አቀባዩ፣ ሌላ ጊዜ በአምባሳደሮች፣ ደስ ሲለው ደግሞ ስልጣን ለቀዋል በተባሉ ሰዎች የተምታታ መግለጫ ከሚያስነግር ይልቅ ፣ ህዝቡን ለማረጋጋትም ሆነ የኢሳትን ዜና ለማስተባበል መለስ ዜናዊን በአካል አቅርቦ ለህዝብ እንዲያሳይ፣ ይህን ማድረግ እስካልቻለ ጊዜ ድረስ በተደጋጋሚ መግለጫዎች በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረውን ትርምስም ሆነ በህዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን አለመረጋጋት ለማስቆም አይቻልም ብሎአል።

በረከት ኢሳት ዜናው ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያደርግ የቅንብር ስራ አልሰራም ብለው ከመውቀስ፣ እጅግ ቀላሉ መንገድ " ይህው መሪያችን" ብሎ ማሳየት ነው ያለው ኢሳት፣ አሁንም የኢትዮጵያ መንግስት ለህዝቡ በተለይም ለራሱ ደጋፊዎች ሲል መለስን አቅርቦ በቴሌቪዥን እንዲያሳይ ጠይቋል።

እነ በረከት እንደሚሉት ሳይሆን፣ ኢሳት ለኢትዮጵያ ህዝብ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት የገባውን ቃል መቼውንም ጊዜ ቢሆን እንደማያጥፍ የገለጠው ቦርድ፣ የመለስ ዜናዊን መታመም ኢሳት ይፋ ባደረገበት ወቅት ሽመልስ ከማል በሰጠው መግለጫ “ይህ ኢሳት የፈጠረው የውሸት ወሬ ነው” ብሎ እንደነበረና ውሸትን በመናገር " የውሸት መታወቂያ" የተሰጠው አካል ማን እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ያውቀዋል ብሎአል።

ከዚህም በተጨማሪ ሪፖርተር የተባለው አፍቃሪ ወያኔ ጋዜጣ በትናንትና እትሙ “የኢሳት ድረገጽ የተቋረጠው ከዜናው ጋር በተያያዘ ነው” የሚል ዘገባ ማውጣቱ ታአማኒነት እንደሌለውና ሃቁ ግን በመላው አለም የሚገኙ ጎብኝዎች የኢሳትን ድረገጽ በአንድ ጊዜ በመጎብኘት የመስመር መጨነናነቅ በመፍጠራቸው አገልግሎቱን የሚሰጠው ድርጅት የጎብኝዎች ቁጥር ከስምምነቱ በላይ በመሄዱ ስርጭቱን ለማቋረጥ መገደዱና ይህም ችግር በተከሰተ በ24 ሰአት ውስጥ ተቃሎ ወደ አገልግሎት መመለስ መቻሉ ነው ብሎአል።

ኢሳት የመለስ ዜናዊን ሞት በተመለከተ መረጃውን በአለማቀፍ የአደጋ ተንታኝ በእንግሊዘኛው አጠራር ICG ውስጥ ከሚሰሩ ታማኝ ምንጮች ማግኘቱን መግለጡን እንዳልሸሸገ ገልጾአል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የህወሀት አባላት የ መለስ የጤንነት ሁኔታ እንዲነገራቸው ግፊት መጀመራቸው ታውቋል። በርካታ የድርጅቱ ከፍተኛ ካድሬዎች፣ በህዝቡ ውስጥ ያለው አለመረጋጋት እየጨመረ በመሄዱ ውድባችን ወይም ድርጅታችን እውነታውን ያስታውቀን በማለት ለነባር ታጋዮች ጥያቄ እያቀረቡ ነው ሲል ኢሳት ዘግቦአል።

## የመለስ ዘመን “ዘመነ-መንሱት”

ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ኢትዮጵያችን ከመለስ ዜናዊ ጋር መከራዋ በዝቶ፤ የህዝቧ ሮሮ ወደርና ወሰን አጥቶ፤ ወንዶችና ሴቶቹ ልጆቿ ለስደት ተዳርገው፤ የቀሩትም ዜጎቿ ብሶታቸውን በውስጣቸው ይዘው እንደተዳፈነ እሳት እየጨሱ የኖሩበት አገር ነበረች። እንዲህም በመሆኑ እንደ አገር የመቀጠሏ ሁኔታ ከፍተኛ ጥራጣሬ ውስጥ ገብቶ ለመፍረስ አደጋ ላይ ያለች አገር ለመባል በቃች።

መለስ ዜናዊ የነበረባት ኢትዮጵያ ከድሆች ጉሮሮ እየተዘረፈ በውጭ አገራት ባንኮች የተደበቀው የዶላር መጠን ከ11 ቢሊዮን ዶላር በላይ መሆኑን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያጋለጠበት ዘመን ነበር። ይህን ዝሪፊያ በተመለከተ በዝሪፊያው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳተፈው መለስ ዜናዊ አንዳችም ቃል ሳይተነፍስ ክሱን በዝምታ ማለፉ ብዙዎችን ጉድ ያሰኘ ነገር ነበር።አገራችን በታሪኳ ይህን የመሰለውን ዝሪፊያ ስታይ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመጀመሪያው ነው።

የመለስ ዜናዊ የዝሪፊያ አንጃ በዚህ ብቻ አያበቃም።ገበሬው ክረምትና በጋ ሳይለይ በብዙ ድካም ካመረተው ቡና ውስጥ ዘጠኝ ሚሊዮን ኪሎ ግራሙ የት እንደገባ ሳይታወቅ ቀርቷል፤ ከአገሪቷ ብሄራዊ ባንክ ውስጥም ብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ወርቅ ተሰርቆ በባሊስትራ ተተክቶ ተገኝቷል። ከአገሪቷ ባንኮች ውስጥ ያለምንም ማስያዣ በብድር ስም እየወጣ “እኛ ወርቆች ነን” ብለው ራሳቸውን ለሚጠሩ ቡድኖች ሲከፋፈል ሌላው ግን ጦሙን እንዲያድር የተደረገበት አገር ነበረች።

የመለስ ነውር ይሄ ብቻ አይደለም በአገሪቷ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከ61 ጄኔራሎች መካከል 58ቱ ከአንድ ብሄረሰብ(ከትግራይ) ብቻ ተመርጠው ተሹመው ሌሎች የኦሮሞ፤ የአማራና የሌሎች ብሄር አባላት ጄኔራሎች ገሚሶቹ ለስደት የተዳረጉበት፤ ገሚሶቹ በየወህኒ ቤቱ እንዲማቅቁ የተደረገባት አገር ነበረች።

ከመለስ ጋር የነበረች ኢትዮጵያ ከየትኛውም ግዜ በተለየ መልኩ ህግ ዜጎችን ለማጥቂያነት ጥሩ መሳሪያ የሆነባት፤ ፍትህም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መሳቂያ መሳለቂያ ሁኖ እንዲዋረድ የተደረገበት አገር ነበረች።

ህግ ዜጎችን ማጥቂያ መሣሪያ በመሆኑ ራሱን ጣኦት አድርጎ የሳለውን መለስ ዜናዊን ተችቶ መናገርም ሆነ መጻፍ በአሸባሪነት አስከሥሶ የሞት ፍርድ የሚያስፈርድ ወንጀል የሆነባት አገር ነች ኢትዮጵያ። ለምን ተናገራችሁ ፤ለምንስ ጻፋችሁ ተብለው በመለስ ዜናዊ ዘመን በአሸባሪነት ተከሰው በየወይኒ ቤቱ የሚማቅቁት ድንቃ ድንቅ የአገሪቷ ልጆች ህግ ዜጎችን ለማጥቂያነት መዋሉን የሚያሳዩ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

መለስ ዜናዊ ያለባት ኢትዮጵያ ዜጎች የአምልኮ ነጻነታቸውን ተነጥቀው መንግስት የምታመልኩትን እኔ እመርጥላችኋለው ብሎ የአምልኮ መንገድ እስከመምረጥ የተደረሰበት አገር ነች። በዚህም እኩይ ድርጊታቸው ብዙ የእስልምና እምነት ተከታይ ንጹሃን ዜጎች በቆመጥ ተደብድበዋል፤ ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ አማኞችም ተገድለዋል፤ ተወዳጅ የሃይማኖቱ መሪዎቹም ዜጎችን ለማጥቂያነት በተሰራው ህግ ተከሰው አሸባሪ ተብለው ለእስራት ተዳርገዋል።

መለስ ዜናዊ ይመራት የነበረችው ኢትዮጵያ ምንነቱ ባልታወቀ ጦርነት ውስጥ ገብታ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ልጆቿን ያጣች አገር ነበረች። በዚህ ምንነቱ ባልታወቅ ጦርነት ውስጥ ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆች፤ ባሎቻቸውን የተነጠቁ ሴቶች ፤አባት አልባ ሆነው የቀሩ ልጆች ከዚህ ጦርነት በኋላ አገሪቷ ምን አተረፈች ብለው ቢጠይቁም መልስ የሚሰጥ መሪ ያጡበት አገር ነበረች።

የመለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ራሳቸውን ወርቅ ብለው የሚጠሩ ጥቂት ዘረኞች ደምና አጥንታቸውን ቆጥረውና ተደራጅተው አገሪቷን ያራቆቱበት፤ ዜጎችን ለርሃብ ለእርዛት ለጉስቁልናና ለስደት የዳረጉበት፤ ዜጎች በገዛ አገራቸው መኖር ባለመቻላቸው ወደማያውቁበት ባእድ አገራት ተሰደው መከራቸውን እንዲያዩ የሆኑባት አገር ነበረች።

የመለስ ዜናዊን ዘመን መከራና ስቃይ ቆጥረን አንዘልቀውም። አገሪቷ የገባችበትን አዝቀት ተናግረን አንጨርሰውም። እንዲያው በደፈናው የመለስ ዜናዊ ዘመንን ዘመነ መንሱት ብለነው እናልፋለን።

መለስ ዜናዊ በዘመኑ ብዙ አሾሆችን በየቦታው ተክሏል። ግዜያቸውን ጠብቀው ሊፈነዱ የሚችሉ ቦንቦችንም በአገሪቷ ጥጋ ጥግ ላይም ቀብሯል።በስንዴዎች መካከልም ብዙ እንክርዳዶችን ዘርቷል። የተቀበረው እሾህ ዜጎችን እንዳይወጋ፤ቦንቡም ፈንድቶ ብዙ ጥፋት እንዳያደርስ፤ እንክርዳዱ የስንዴውን ዘር እንዳያጠፋ ዜጎች እጅ ለእጅ ለመያያዝ መልካሙ ግዜ አሁን ነው። አገሪቷና ህዝቦቿ በዚህ ሁኔታ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሁነው ለነጻነት፤ ለፍትህ እና ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለመተባበር ፈቃደኛ የማይሆን ቡድንም ሆነ ግለሰብ መከራችንን ከሚያበዛው ከህወሃት በምን እንደሚለይ ራሱን ይጠይቅ።

መለስ ዜናዊ ያመልኩት ዘንድ በዙሪያው የሰበሰባቸው ደካማ ዘረኞች አገሪቷ በምን መልኩ መመራት እንዳለባት ለመወሠን ይሄ ነው የሚባል አቅም ያላቸው አይደሉም። የህዝቡንም ድምጽ ለማዳመጥ የታደሉ አይደሉም። ቁሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟለት ከመሯሯጥ የዘለለ ሌላ ምኞትም አልነበራቸውም ዛሬም የላቸውም። እንዲያውም የዘረፉትን ገንዘብ የሚያሸሹበትን ሥፍራ ፍለጋ ላይ ተጠምደው መሰነበታቸውን በተለያዩ መንገዶች የደረሱን መረጃዎች እያሳዩን ይገኛሉ።

አገራችን ኢትዮጵያ መለስ ዜናዊ ሲመራው ከነበረው ህወሃት ከተባለው ዘረኛ እና ዘራፊ ቡድን ጋር እድሏ የጨለመ ሆኖ ስንብቶአል ። ከእነዚህ ጥቂት ዘረኛ ቡድኖች እጅ አገራችንን የማላቀቅ የዜግነት ግዴታ አለብን። መለስ ዜናዊ “ይህች አገር” እያለ ከሚጠራት ኢትዮጵያችን ተገለለ ማለት የተከላቸው መርዞች ሁሉ ተወገዱ ማለት አይደለም። መለስ ዜናዊ የዘራቸው የጥላቻ ዘሮች ለምሳሌ “አማራ የትግራይ ቀንደኛ ጠላት ነው” ብሎ ያስተማረውን እኩይ ትምህርት በልባቸው ጽላት ጽፈው አማራን አርቀን እንቀብራለን የሚሉ ገልቱ ግለሰቦች እስከ አሁን የስልጣኑን ወንበር እንደያዙ አሉ። ውሸትን እንደ እውቀት የሚቆጥሩ፤ ውሸታቸውንም እውነት ነው ብለው የሚያምኑ በሽተኞች እስከ አሁን በቤተ-መንግስት ውስጥ አሉ። ህዝቡን በሃይማኖት እና በብሄር ከፍለው በአንዲት አገር ዜጎች መካከል መተማመን እንዳይኖር ብቻ ሳይሆን የእርስ በእርስ ግጭት ተነስቶ ህዝቡ ደም እንዲቃባ ለማድረግ ቆርጠው የቆሙ ቡድኖች በትረ-ስልጣኑን እንደያዙ አሉ። ህግን ቂመ መወጣጪያ በማድረግ የአገሪቷን የፍትህ ሥርዓት ለማዋረድ ግንባራቸውን ሳያጥፉ ተግተው የሚሰሩ ቡድኖች እስከ አሁን በህይወት አሉ። ይህ ለአገራችን ከባድ ፈተና ነው።

አገራችን እንዲህ ባለው ፈተና ውስጥ እያለች ለችግሩ የጋራ መፍትሄ ለማግኘት አብሮ ተባብሮ እና ተቻችሎ ከመታገል ውጪ የተሻለ አማራጭ የለንም።ለነጻነት ለፍትህና ለእኩልነት ከሚታገል ከማንኛውም ቡድን ጋር ተባብረን ለመታገል ያለን አቋም አይለወጥም። ግንቦት ሰባት የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል እንጂ ወደ ኋላ አይልም። ዜጎች ሃይማኖታቸውን በነጻነት መከተል እስከሚችሉ ድረስ፤ የመጻፍ እና የመናገር መብት ያለምንም መሸራረፍ በኢትዮጵያችን ከአጽናፍ አሰከ አጽናፍ እስከሚረጋገጥ ድረስ፤ የግለሰቦች መብት ያለ ምንም ገደብ በመላዋ ኢትዮጵያ እስከሚሰፍን ድረስ የጀመርነውን ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን እንጂ አናፈገፍግም። የጀመርነውን ትግል በድል ሳንቋጭ የሚያቆመን ምንም ነገር የለም። ደግሞም እውነት ከእኛ ጋስ ስለሆች እናሸንፋለን። በዚህም ደስ ይለናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

## ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተቀሰቀሰዉ የጎሳ ግጭት አሁንም እልባት

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የሚተዳደረዉ ህብረተሰብ ደግሞ ዉሀና ግጦሽ ፍለጋ በሦስቱም አገሮች ዉስጥ የሚመላለስ ስለሆነ በአብዛኛዉ በጦር ሜዳ መሳሪያዎች የታጠቀ የራሱ የሆነ ሚሊሺያ ያለዉ ህብረተሰብ ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔ አገዛዝ ሶማሊያ ዉስጥ የተፈጠረዉንና ለብዙ አመታት የዘለቀዉን መንግስት አልባነት አስመልክቶ በቦረና አካባቢ የሚኖሩትን የጋሪ ብሔረሰቦች በከፍተኛ ደረጃ ያስታጠቀ መሆኑ ግጭቱን አደገኛ አድርጎታል። በዚህም የተነሳ ይህ በገጠር አካባቢ የተቀሰቀሰዉ ግጭት በፍጥነት ተቀጣጥሎ የአካባቢዉን ትልቅ ከተማ ሞያሌን ስጋት ላይ ጥሏት እንደነበር ከስፍራዉ የደረሰን ዜና ያስረዳል። ኬንያና ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የቀይ መስቀል ምንጮች እንደገለጹት ከግጭቱ ለመሸሽ ከአካባቢዉ የሚሰደደዉ ህዝብ ብዛት 20ሺ መድረሱንና ግጭቱ ዘላቂ መፍትሄ የማያገኝ ከሆነ የሚሰደደዉ ህዝብ ብዛት የኬንያን ብሔራዊ ደህንነት ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊጥለዉ አንደሚችል የኬንያ ባለስልጣኖች ያደረባቸዉን ስጋት ከወዲሁ ማሰማት ጀምረዋል።

የቢቢሲና የቀይ መስቀል ዘጋቢዎች የግጭቱ መንስኤ ከመሬት አጠቃቀም ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነዉ ብለዉ ቢዘግቡም የዚህ ሁለቱን ብሔረሰቦች ለሞት፤ለአካል ጉዳትና ለስደት የዳረገዉ ግጭት መሠረታዊ መንስኤ ወያኔ የፈጠረዉ የጎሳ ፌዴራሊዝም መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። አብሮና ተቻችሎ ጎን ለጎን መኖርን ሳይሆን የተለያዩ ብሔረሰቦችን በጎሳ አጥር ከፋፍሎና ለያይቶ ያስቀመጠዉ የወያኔ የጎሳ ፌዴራሊዝም ለዚህ የሰሞኑ ግጭት ብቻ ሳይሆን ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከለ ለደረሰዉ ደም መፋሰስ በዋነኛነት የሚጠቀስ ምክንያት ለመሆኑ ብዙ ጥናታዊ ዘገባዎች በመረጃ አስደግፈዉ ያስቀመጡት ሐቅ ነዉ። ለዚህም በደቡብ ክልል በጉጂና በጌዲኦ፤ በጉጂና በቡርጂ፤ጋምቤላ ዉስጥ በኑርና በአኝዋክ፤ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ በኦሮሞና በሶማሊያ ምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ በኦሮሞና በጉሙዝ እንዲሁም በአማራና በጉሙዝ ብሔረሰቦች መካካል የተቀሰቀሱት ግጭቶች ሊጠቀሱ የሚችሉ አይነኛ ምክንያቶች ናቸዉ።

## ቱባው የወያኔ አሊቃ ስብሃት ነጋ የመለስ ዜናዊን ህመም አስመልክቶ ህዝቡ እኔ የሰጠሁትን አስተያየት ትቶ ማመን ያለበት የበረከትን ነው ሲል ለቅጥፈቱ ይቅርታ እንኳን ሳይጠይቅ ደረቱን ነፍቶ ገለጸ

ስብሃት ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ የሁለታችን መግለጫ የተለያየ ቢሆንም የግድ መመሳሰል የለበትም እናም የኔን ትታችሁ የበረከትን ተቀበሉ ብሏል።

በማያያዝም በአሁኑ ወቅት አጠገቡ ካሉ ሰዎች እንደምሰማው ጤንነቱ እየተሻሻለ ነው ያለው ስብሃት የዘረኝነትና የጥላቻ ፖለቲካ ዋነኛ አጋሩ መለስ አውሮፓ መኖሩን እንጂ የት ሆስፒታል እንደሚታከም እንደማያውቅ በመጥቀስ ሰሞኑን ሪፖርተር ጋዜጣ አሜሪካን በእረፍት ላይ ነው ሲል ያወጣው ቅጥፈት መሰረተ ቢስ መሆኑን አመላክቷል።

ግንቦት 7 በሰሞኑ ዜናው ሪፖርተር ጋዜጣ ያወጣው መለስ በአሜሪካን እረፍት ላይ ነው የሚለው ዘገባ ፍጹም ውሸት መሆኑንና በቤልጂየም ሴንት ሉክ ሆስፒታል ውስጥ እየታከመ እንደሚገኝ መዘገቡ ይታወሳል። ቅጥፈትን እንደ ትልቅ የፖለቲካ እውቀት ለሚያዩትና ማጭበርበርን ለሚኮሩበት ወያኔዎች እርስ በእርሱ የሚቃረን መግለጫ መስጠት ምንም ባይመስላቸውም ህዝቡ ግን መቼ ነው ከወያኔዎች የሚታመን መረጃ ማግኘት የምንችለው በማለት መጠየቁን ቀጥሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የትግራይን ህዝብ ያናድዳል ብሎ የሚያስበውን ከመፈጸም ወደ ኋላ የማይለው ስብሃት አድዋ የሚገኘው የንግስተ ሳባ ትምህርት ቤት 70ኛ ዓመት ክብረ በዓል ሲከበር የቀድሞውን የደርግ ዘመን ምክትል ፕሬዘዳንት ኮሎኔል ፍስሃ ደስታን አስከትሎ በመሄድ ብዙዎችን ማናደዱ ታውቋል።

በወቅቱ በቦታው ምን ስሜት እንደተፈጠረ ከጋዜጣው ለቀረበለት ጥያቄ ለእኔ በግልጽ ወጥቶ የነገረኝ የለም፤ አንዳንዶች ቅር ሊላቸው ይችላል፤ ይሁንና ደስ ያለኝን አድርጊያለሁ ብሏል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በፈጠረው ጸረ ኢትዮጵያዊ ጥቃት ከአገራቸው ይልቅ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ጋዜጣው ይፋ እንዳደረገው መረጃ በርካታ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በወያኔ አገዛዝ በሚደርስባቸው በደል በመማረር ዜግነታቸውን እየቀየሩ ለሌሎች አገሮች መሰለፍ ከጀመሩ ውሎ አድሯል።

ለምሳሌ ባህሬን ለለንደኑ ኦሎምፒክ አስራ ሁለት አትሌቶችን ያሰለፈች ሲሆን ከእነዚሁ ሰባቱ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። በለንደን ኦሎምፒክ ባህሬንን ወክለው የሚሰለፉ ኢትዮጵያዊያን ስምዝርዝር ፤

1ኛ ገንዘብ ሹሚ
2ኛ ቢሊሱማ ሹጊ
3ኛ ማርያም የሱፍ ጀማል (ዘነበች ቶላ)
4ኛ ሽታዬ እሽቴ
5ኛ ሊሻን ዱላ
6ኛ ሚሚ በለጠ
7ኛ ታጁ ዲባ

በዚሁ በለንደሉ ኦሎፒክስ ሁለት ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለአዘርባጃን ይሮጣሉ። እነሱም

1ኛ ለይስ አብዱለ ይቫ በ5000 ሜትር ሴቶች
2ኛ ኃይሌ ኢብራሂም በ5000 ሜትር ወንዶች

በተመሳሳይም ቤተልሄም ደሳለኝ በ1500 ሜትር የተባበሩት የአረብ ኤመረቶችን ወክላ ትወዳደራለች።

ለኦሎምፒክስ ውድድር የሚያበቃቸው ሚኒማ ባለሟሟላታቸው በለንደን ኦሎምፒክስ ባይካፈሉም በተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ውድድሮች በመሳተፍ ዓለም ዓቀፍ ዝና ያተረፉ ዜግነታቸውን የቀየሩ አትሌቶች ቁጥራቸው በ30 በላይ እንደሚገመት ዘሃበሻ ጋዜጣ ገልጿል።
እነርሱም

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ቢሊሱማ ሱፔ | ባህሬን | 13. | በዛብህ ሲሳይ | አውስትራሊያ |
| 2. | ደጀኔ ረጋሳ | ባህሬን | 14. | ባደርካህሊል ባደር | ባህሬን |
| 3. | አላፍ ቢምሮ | እስራኤል | 15. | ሳሌዝ ማርኩት | ባህሬን |
| 4. | ሰጠኝ አበበ | እስራኤል | 16. | ዘነበች ቶላ | ባህሬን |
| 5. | ዋደሬ ሃቭዳያ | እስራኤል | 17. | እድሪስ ካማል | ባህሪን |
| 6. | ኤልናብ አብይ ለገሰ | ቱርክ | 18. | ያሬድ ሰጉሞ | ፓላንድ |
| 7. | ተክዬ ገ/ሥላሴ | ሆላንድ | 19. | ገነሺ ታምራት | እንግሊዝ |
| 8. | ኡ ዜሪዬተ ታምራት | ቱርክ | 20. | ቶማስ አብዩ | እንግሊዝ |
| 9. | ደጀኔ ብርሃን | እንግሊዝ | 21. | አየማየሁ በዛብህ | ስፔን |
| 10. | ሚዛን መሃሪ | አውስትራሊያ | 22. | ሰለሚ ባይራክ | ቱርክ |
| 11. | ካሳ ታደሰ | እንግሊዝ | 23. | ሱልጣን ሃይደር | ቱርክ |
| 12. | ኤርባህ ሙስተፋ | ጣልያን | 24. | የሺጥላ በቀለ | ቤልጅየም |

25. ማዲና ከድር የተባበሩት የአረብ ኤምሬቶች ከድር
26. ማርያም አብዱላሂ የተባበሩት የአረብ ኤምሬቶች

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ኢትዮጵያ አገራችንን በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች በመልካም ሥም የሚያስጠሩዋትን አትሌቶች እንዲሰደዱ በማድረግ እስከ ዛሬ አገራችንን ከመሩዋት አምባገነኖች ሁሉ የተለየ ሆኖአል።

## በአዲስ አበባ እንደ ወረርሽኝ በመጡት የእርቃን ዳንስ ቤቶች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለዚህ ማህበራዊ ቀውስ መባባስ የጫት መቃሚያ፣ የሺሻ ማጨሻ፣ የጭፈራና የዳንስ ቤቶች መስፋፋት ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ በመግለጽ በአሁኑ ወቅት እነዚህ ጉዳዮች የሚፈጸሙባቸው 3ሺህ 691 ቤቶች በአዲስ አበባ እንደሚገኙ አንድ ሌላ ጥናት ማመላከቱን አፍቃሪ ወያኔው ሪፖርተር ዘግቧል።

በተለያዩ የሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ልቡናዊ ዘርፎች የተደረጉ ጥናቶች በሁሉም መስኮች የወያኔ ስርዓት መጠገን በማይችልበት ሁኔታ መበስበሱን የሚያመላክቱ ሲሆኑ ይህም ጥናት ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

**ከሀገሬ ነጎሴ 2000 ዓ.ም.**

ኽረ እነግርሃለሁ አይደለንም ጀግና
ዓለም ያደነቀን እኛን መች ሆነና

በአያት ቅድም አያት በጥንት ታሪካችን
በእርግጥ ተከብረናል በጀግንነታችን

አልዋሸህም እኔ ያ እኮ ድሮ ቀረ
ለሀገር መሰዋት ጀግንነት ነበረ

ዛሬ ግን እውነቱ ካላልን እንዋሽ
ጀግኖች አይደለንም በፍፁም በጭራሽ!

ምናልባት ሆነን እንደው የጀግኖቹ ልጅ
አልያም ከሆንን የጀግኖች የልጅ ልጅ

ከሆነ ነው እንጂ እኔ አልስማማም
ጀግና ባሁን ዘመን ኽረ ፍፁም የለም
አትንደድ በቁጣ አይጣልህ በሽታም
ይህ እውነታ ነው ጀግናስ ዛሬ የለም

ብንሆንማ ጀግና ልክ እንዳባቶቻችን
ዝም አንልም ነበር ሲሸጥ መሬታችን

እስቲ አንተ ንገረኝ የታል ጀግንነቱ
ማንስ ምን አረገ ሲወሰድ መሬቱ

እባክህ ወንድሜ ጀግኖቹን ተዋቸው
ነቅተው እንዳያፍሩ አትቀስቅሳቸው

ዝም እንበል እኛ እነሱን አናንሳ
መሆን አቅቶናል እንደነሱ አንበሳ

በል እስቲ ንገረኝ አንተ የጠየከው
ወለላዬ አልከኝ ከስዊድን ያለኸው

እውነት ጀግና ብንሆን ዓለም ያደነቀን
እንተኛ ነበር አሁን በዚህ ዘመን
የቋራው መሬት ሲወሰድ እያየን

ሊያውም የጀግናችን የቴዎድሮስ ካሣ
ለሀገሩ የሞተው ለሕይወቱ ሳያሳሳ

ስለዚህ ወንድሜ ብትወድም ብጠላም
ዋጥ አርገው እውነቱን ጀግናች አይደለንም!

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org